EthioLion

# መለስ ሲሸማቀቅ

እ.ኤ.አ. ግንቦት ቀን 2012 ዓ.ም. በ ጅ 8 ስብሳባ ላይ ታዋቂ የአለም መሪዎች በተገኙበት ጠቅላይ ሚኒስትራችን መለስ ዜናዊ የልመና ኮሮጆ ይዘው ተገኝተው እንደነበር ይታወሳል።

ለዚህም ማጠናከሪያ እንደተለመደው የኢትዮጵያን ህዝብ ልብ የሚያደማ አሀዝ ሊተነትኑ ሲጀምሩ ውድ የኢትዮጵያ ተቆርቋሪና የወገን ብሶት አስተጋቢ የሆነው ጋዜጠኛ አበበ በለው ስማቸውን ጠርቶ የአገዛዙን አስከፊነት በመረዋ ድምፁ ሲያስተጋባ በሀይል የተሸማቀቁት መሪያችን ጉዳይ ውስጤ ስለገባ ከዚህ በታች ያለችውን ስንኝ ቋጠርኩላቸው።

አገሬ ከስዊድን
2012/05/19

አበበ አሸባሪው ፤ እንዳለው መለስ
ውነት አሸባሪ ፤ እንደመለስ ክስ
ፈንጅ ሳይታጠቅ ፤ ጥይት ሳይተኩስ
የወገኑን ጠላት ፤ ምርጡና ባንዳውን ፤ አረገው ኩስስ ።




አቤ ኢትዮጵያው ፤ ድምፁን ስላሰማ
መለስ ፈሪ ሆኖ ፤ ቦቅቧቃ ደካማ
ውርደቱ ቅሌቱ ፤ በአለም ተሰማ ።

ከኢትዮጵያውያን ፤ ከሌላው ዘር በልጦ
ምርጥ ዘር እያለ ፤ በጥጋብ ተንጦ
በልቡ ያለውን ፤ ትቢት አስበልጦ
በአለም አደባባይ ፤ ሸንጎ ተቀምጦ
በድምፅ ሲበረግግ ፤ ሲታይ ተንቀጥቅጦ
ምን ይላል አደዋ!  በመለስ ተሰጦ
ይኮራ ይሆን ወይ?  ምርጡን ፈሪ መርጦ።

ዘረኛው ወያኔ ፤ መለስ መለስ ሲል
ቀልቡ ተገፈፈ ፤ በውነተኛ ቃል
ህዝብ ሲያሸማቅቅ ፤ ንቀት ሲያስተጋባ
በአለም አደባባይ ፤ ጥፍሩ ውስጥ ገባ ።

ውነት እንዲህ ያማል ፤ ሲነገር በይፋ
ሰማኒያ ሚሊዮን ፤ በስቃይ ሲገፋ
ዛሬ ቀኑ ደርሶ ፤ መለስም ተከፋ ።

ፈርቶ የሚያስፈራ ፤ የፈሪዎች ቁንጮ
በድምፅ ተደናብሮ ፤ አየነው ቀጭጮ
ይች ጅምሯ ናት ፤ ትንሿ መቀጮ።

መለስ አይሳይ ነው ፤ ልመና በመላ
ደግሞ ብሎ ብሎ ፤ የአገር አንጀት በላ ።

ታላቅ የመሰልከው ፤ ፈሪ የእኔ ቢጤ
ድንብርብር ስትል ፤ በዚያ ድንጋጤ
ጠብ አለ ወይ ከታች? በፍርሀት መጤ ።

Ethiopia Will Prevail!